# በኒው ሳውዝ ዌልስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር

## ባለ አደራ ኮሚቴ መተዳደሪያ ደንብ

### መግቢያ

በኒ.ሳ.ዌ. የኢት. ኮ. ማ. ከተመሰረተ አያሌ አመታትን አስቆጥሯል። ይሁን እንጂ ማህበሩ ካሳለፈው ሁለት አስርታት አንፃር በንብረትም ሆነ በካፒታል ይዘት ሲገመገም ገና በእንጭጩ ያለ ማህበር ሆኖ ይገኛል።

ለዚህም አቢይ ምክንያቱ የአሰራር እና የንብረት ቁጥጥር አለመኖሩ ሲሆን በተለያየ ጊዜ ወደ ማህበሩ የሚመጡ የማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴዎችም ይህንን መሰረታዊ ድክመት እስከዛሬ ሊቀጩት አልቻሉም።

ከዚህ በተጨማሪም የማህበሩ እንቅስቃሴ በተወሰነ ዘመን ሞቅ፤ ደመቅ ይልና በተወሰነ ዘመን ደግሞ ደብዛው ይጠፋል። ይህ የአሰራር ወጥነት አለመኖር የማህበሩ ሌላው አቢይ ድክመት ነው። ከዚህ ሌላ አዲስ የስራ አመራር ኮሚቴ ሲመረጥ ቀድሞ የተጀመሩ ስራዎችንና እቅዶችን አዳብሮና አዲስ እቅዶችን አክሎ ማህበሩን በንብረትና በካፒታል ከማሳደግ ይልቅ የተጀመሩ ተግባራትን ደምስሶ አዲስ ተግባር (ተግባራት) ላይ ማተኮር፤ ማህበሩ ያለውን ካፒታል በተወሰነም ደረጃ ቢሆን ከፍ አድርጎ ለቀጣዩ የስራ አመራር ኮሚቴ ከማስረከብ፤ ያለችውን ውድምድም አድርጎ ባዶ ካዝና ማስረከብ፤ ንብረቶቹን ተንከባክቦና ተቆጣጥሮ አለመያዝ እና አለማስረከብ፤ የተጠያቂነት የውዴታ ግዴታ (አካውንቴብሊቲ) መኖሩን አለመገንዘብ፤ ለማህበሩ ህገ ደንብ (ኮንስቲትዩሽን) አለመገዛትና ሃላፊነትን በህገ ደንቡ መሰረት ያለመወጣት በማህበሩ የቆዩ አሰራር መሰረታዊ ችግሮች ሆነው ተስተውሏል።

ከአመታት ልምድ እንደታየው ማህበሩ በዚህ አካሄድ ብልጭ ድርግም ከሚል እንቅስቃሴ ውጪ ቋሚና ተከታታይ ተግባራትን በመፈፀም፤ ማህበሩን በተለያዩ ንብረቶች በማደርጀት፤ የመንቀሳቀሻ ካፒታሉንም በማሳደግ፤ ህብረተሰቡን ይበልጥ የሚያገለግሉ መርሃ ግብሮችን (ፕሮጀክቶችን) ለመንደፍና ለመተግበር፤ ወጣቱ ትውልድም የዚህ ማህበር ተጠቃሚና ተረካቢ እንዲሆን ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፤ እስከዛሬ የቆየውን የአሰራር መንገድ መቀየር ለማህበሩ እድገትና ጤናማ ህልውና አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ከላይ እንደ መነሻ የቀረቡትን ድክመቶች ለመቅረፍ፤ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ (ኮንስቲትዩሽን) የተገለፁትን የማህበሩን ተግባራት በብቃትና በጥራት ለመወጣት፤ ያሉትን ንብረቶች ከብክነት ለመከላከልና ተጨማሪ ንብረቶችንም በ አግባቡ ለመጠበቅ፤ ካፒታሉን ለማሳደግና ያለውንም ከአላስፈላጊ ጥፋት ለመጠበቅ፤ በየወቅቱ በስራ አመራር ኮሚቴ አባላት መካከል በሚፈጠር (ሊፈጠር በሚችል) ግጭት ሳቢያ የማህበሩ እንቅስቃሴ እንዳይበደል፤ ህልውናውም አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ለመከላከል የማህበሩን ባለ አደራ ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኗል።

## 1. በኒ.ሳ.ዌ.የኢት. ኮ. ማ. ባለ አደራ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር

1.1. በማህበሩ አጠቃላይ ጉባኤ የሚሰየመው ባለ አደራ ኮሚቴ ሶስት አባላት ሲኖሩት ኮሚቴው የማህበሩን ዘላቂ ህልውና እና ጥቅም ከአደጋ የመከላከልና የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት።

1.2. በማህበሩ ህገ ደንብ (ኮንስቲትዩሽን) መሰረት በተመረጡ የማህበሩ የስራ አመራር ከኮሚቴ አባላት መካከል አለመግባባት ቢፈጠርና ይህም የ ኮሚቴውን እንቅስቃሴ የሚገድብ ሲሆን የማህበሩ ፕሬዚዳንት ጉዳዩን ለባለአደራ ኮሚቴ ያቀርባል። ባለአደራ ኮሚቴውም የስራ አመራር ኮሚቴውን በመሰብሰብ ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ይመክራል።

1.3. ከላይ በ1.2. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በስራ አመራር ኮሚቴው መካከል የተፈጠረውን ችግር ማስወገድ ካልተቻለና የማህበሩ እንቅስቃሴ የሚበደል ሆኖ ከተገኘ ባለአደራው ኮሚቴው የማህበሩ አጠቃላይ ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል።

1.4. በ1.3. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚጠራው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ መድረኩን የሚረከበው ባለአደራ ኮሚቴ ሲሆን ችግሩን ለምልአተ ጉባኤው በማቅረብና በማወያየት ጉባኤው በሚያስተላልፈው ውሳኔ መሰረት የማያዳግም እልባት እንዲሰጥ ያደርጋል።

1.5. የስራ ጊዜያቸውን ባጠናቀቁ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ምትክ አዲስ ኮሚቴ ለማስመረትጥ ባለአደራ ኮሚቴ ባስመራጭነት ይሰራል፡ መድረኩንም ከተሰናባቹ የስራ አመራር ኮሚቴ በመረከብ ምርጫውን ለማካሄድ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ይወስናል። አዲሱን ኮሚቴም ያስመርጣል።

1.6. ባለአደራ ኮሚቴ የማህበሩን ቋሚ ንብረቶች ዝርዝር ሰነድ ይይዛል።

1.7. የስራ ጊዜያቸውን በጨረሱትና አዲስ በተመረጡት የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት መካከል በመገኘት የማህበሩ ዶክመንት፡ ንብረታና፡ ካፒታል ርክክብ እንዲካሄድ ያደርጋል።

1.8. በ1.7. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በርክክቡ ወቅት ባለ አደራ ኮሚቴው በእጁ ከሚገኘው የማህበሩ ንብረት ሰነድ ዝርዝር ጋር ካስረካቢው የስራ አመራር ኮሚቴ የንብረት ዝርዝር ጋር በማመሳከር ላዲሱ ኮሚቴ የማህበሩን ንብረት ያስረክባል። የርክክቡንም ሰነድ ተሰናባቹ ኮሚቴ፡ አዲስ የተመረጠው ኮሚቴና ባላደራ ኮሚቴ ተፈራርመውበት ዋናውን ሰነድ ይይዛል፡ ቅጂውንም ላስረካቢና ተረካቢ ይሰጣል።

1.9. በ1.8. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ በርክክቡ ወቅት የጠፋ የማህበሩ ጥሬ ንብረተ (ቁሳቁስ) ወይም አለ አግባብ የባከነ የማህበሩ ካፒታል (ገንዘብ) ወይም ንብረትና ካፒታል መኖሩ ከተረጋገጠ ባለ አደራ ኮሚቴው ጉዳዩን የመመርመርና የማጣራት ሃላፊነት ሲኖርበት የምርመራው ውጤት እስኪታወቅ ርክክቡን ያዘገያል።

1.10. በ1.9. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ የጠፋው ንብረት/ካፒታል አግባብ ባልሆነ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለ አደራ ኮሚቴው የማህበሩን ምልአተ ጉባኤ በመጥራት ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል።

1.11. የማህበሩን ንብረት/ካፒታል ያባከነው አካል የማህበሩ ጉባኤ በሚያሳልፈው ውሳኔ መሰረት በሰላማዊ መንገድ ንብረቱ/ካፒታሉ ለማህበሩ የማይመለስ ከሆነ ባላደራ ኮሚቴው የጠፋውን የማህበሩን ንብረት/ካፒታል በህገ የመጠየቅ መብት አለው።

1.12. በየወቅቱ በማህበሩ ውስጥ የሚያገለግሉ የስራ አመራር ኮሚቴዎች በስራ ዘመናቸው መጨረሻ ላይ በማህበሩ የሂሳብ አካውንት ውስጥ ተቀማጭ ካደረጉት ገንዘብ 60% (ስልሳ በመቶ) ውን ባለ አደራ ኮሚቴው ይረከባል።

1.13. በ1.12. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ ባለ አደራ ኮሚቴው የተረከበውን ገንዘብ "የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ተራድኦ አካል" (Ethiopian Community Welfare Group) በሚል ስም አካውንት ከፍቶ ተቀማጭ ያደርጋል።

1.14. የማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ ያቀደው ከፍተና ፕሮጀክት ካለና ለዚህም ፕሮጀክት ተፈፃሚነት ገንዘብ ካጠረው ለባለ አደራ ኮሚቴ ፕሮጀክቱንና የብድር መጠየቂያ ሰነድ ማቅረብ ይችላል።

1.15. በ1.14. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ ባለ አደራ ኮሚቴው በቀረበለት ፕሮጀክትና የብድር መጠየቂያ ሰነድ ላይ ለብቻው ወይም ከስራ አመራር ኮሚቴ ጋር በጋራ ተነጋግሮ የተጠየቀው ብድር ከፕሮጀክቱ ፍፃሜ በኋላ ተመላሽ ሊሆን ይችላል ብሎ ካመነበት ብቻ የስራ አመራር ኮሚቴ የጠየቀውን ብድር ባለ አደራ ኮሚቴው ሊፈቅድ ይችላል።

1.16. በተራ ቁጥር 1.15. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አበዳሪው (ባለአደራ ኮሚቴ) እና ተበዳሪው (የስራ አመራር ኮሚቴ) በጉዳዩ መስማማት ካልቻሉ የወቅቱ የማህበሩ ፕሬዚዳንት አጠቃላይ ስብሰባ ይጠራል። ምልአተ ጉባኤው ባለ አደራ ኮሚቴውንና የስራ አመራር ኮሚቴውን ነጥቦች መርምሮ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

1.17. ባለ አደራ ኮሚቴ ከማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ የተረከበው ገንዘብ በማይጠፋበትና በማይከስርበት መንገድ ነገር ግን በተወሰነም ፐርሰንት ቢሆን በእጁ ያለውን ካፒታል ያሳድጋል ብሎ በእርግጠኝነት ባመነበት መንገድ የማህበሩን ካፒታል "ኢንቨስት" ማድረግ ይችላል።

1.18. ባለ አደራ ኮሚቴው በየመቱ በማህበሩ አጠቃላይ ጉባኤ ላይ በእጁ ስለሚገኘው የማህበሩ ገንዘብ እና ወይም ስላደረገው "ኢንቨስትመንት" ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል።

1.19. ባለ አደራ ኮሚቴው ከማህበሩ የተረከበውን ያደራ ገንዘብ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ከተሰጠው ሃላፊነትና ተግባር ውጪ አለ አግባብ ተገልግሎበትና አባክኖት ቢገኝ የማህበሩ ምልአተ ጉባኤ በሚሰይመው አጣሪ ኮሚቴ አማካይነት አስፈላጊው ምርመራና ማጣራት ተደርጎ የባከነው ገንዘብ ወደ ማህበሩ የሚመለስበትን ህጋዊ ርምጃ ይወስዳል።

1.20. ባለ አደራ ኮሚቴው ከ1.1 እስከ 1.19. ከተዘረዘሩት ሃላፊነቶቹና ተግባራቱ ውጪ በማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ ላይ የተለየ ስልጣን የለውም።

## 2. ተጠሪነት

2.1 ባለ አደራ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለማህበሩ ምልአተ ጉባኤ ብቻ ነው።
2.2 የባለ አደራ ኮሚቴን አባል/አባላት ከሃላፊነት የመሻር/የመለወጥ መብት ያለው የማህበሩ ምልአተ ጉባኤ ብቻ ነው።

## 3. የስራ ዘመን

3.1 ባለ አደራ ኮሚቴው የስድስት አመት የስራ ዘመን አለው።
3.2 የባለ አደራ ኮሚቴ አባል ከኮሚቴው አባልነት መሰናበት ሲፈልግ የስንብት ማመልከቻ (አመቺው በሆነ መንገድ) ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል።

## 4. ተፈፃሚነት

4.1. በኒው ሳውዝ ዌልስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ባለ አደራ ኮሚቴ መተዳደሪያ ደንብ ከማህበሩ አጠቃላይ ስብሰባ 60% (ስልሳ በመቶ) አባላት ከደገፉት የማህበሩ ህገ ደንብ (ኮንስቲትዩሽን) አካል ይሆናል።

## 5. የባለ አደራ ኮሚቴን ህገ ደንብ ስለማሻሻል

5.1 በኒው አሳውዝ ዌልስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ባለ አደራ ኮሚቴ መተዳደሪያ ደንብ ከማህበሩ አባላት 51% (ሃምሳ አንደ በመቶ) እንዲሻሻል ወይም እንዲሰረዝ ከጠየቁ ጉዳዩ ለማህበሩ አጠቃላይ ጉባኤ ይቀርባል።

5.2. በ5.1. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ ምልአተ ጉባዔው በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በቀረበው ሀሳብ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## 6. ፅናት

6.1. በኒው ሳውዝ ዌልስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ባለ አደራ ኪሚቴ መተዳደሪያ ደንብ ከ ጁላይ 25፣ 2010 ጀምሮ የማህበሩ ህገ ደንብ (ኮንስቲትዩሽን) አካል ሆኖ እንዲያገለግል በምልአተ ጉባኤው ባንድ ድምፅ ፀድቋል።

ጁላይ 25፡ 2010 ሲድኒ አውስትራሊያ